# የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የግልግል ዳኝነት ጉባዔ አሰራር መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 6/2012 ዓ.ም

### መግቢያ

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6 ስር የተቀመጡት የፍትሐብሔር ኃላፊነቶች አማራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓትን የሚደግፍ በመሆኑ፣

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የፌዴራል መንግስቱ ተቋማት የሚያጋጥማቸውን አለመግባባት የሚፈቱበትን መንገድ እንደሚወስን በመቀመጡ፣

ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የግልግል ዳኝነት ጥያቄ በስፋት እየቀረበ የመጣ በመሆኑ፣

የመንግስት ተቋማት በሚገቧቸው ውሎች አማካኝነት የሚፈጠርን አለመግባባት ፈጣንና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ በመፍታት የህዝብና የመንግስትን መብትና ጥቅም ማስጠበቅ የተቋሙ ኃላፊነት በመሆኑ፤

በንግድ፣ በኢንቨስትመንትና በፍትሐብሔር ጉዳዮች የሚከሰቱ አለመግባባቶችን ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መፍታት መልካም ግንኙነትን የሚጠብቅ፣ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታና ሀገራዊ ልማትን የሚደግፍ በመሆኑ፣

በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ጥናት ላይ እንደተመለከተው በመንግስት ተቋማት መካከል የሚፈጠር የፍትሐብሔር አለመግባባት 100% እንዲሁም ከሌሎች አካላት ጋር የሚኖራቸውን የፍትሐብሔር አለመግባባት 85% በአማራጭ የሙግት መፍቻ ለመፍታት እንዲቻል የአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች አሰራር በዋናው መሥሪያ ቤት፣ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በምድብ ፅ/ቤቶች ደረጃ ወጥነት ባለው መልኩ መዘርጋት የሚያስፈልግ በመሆኑ፣

የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 21(2) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ምዕራፍ አንድ፡- ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የግልግል ዳኝነት ጉባዔ አሰራር መመሪያ ቁጥር 6/2012” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

### 2. ትርጓሜዎችና የጾታ አገላለጽ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ማንዋል ውስጥ፡-

1. **“የግልግል ዳኝነት”** ማለት በዚህ ደንብ መሰረት በሚሾም/ሙና በሚመደብ/ቡ አንድ ዳኛ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ዳኞች በግልግል ዳኝነት ሊፈቱ የሚችሉ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚካሄድ አሰራር ነው፡፡
2. **“በግልግል ዳኝነት ሊፈታ የሚችል አለመግባባት”** ማለት በህግ አግባብ ለግልግል ዳኝነት ሊቀርብ የሚችል ማንኛውም ዓይነት የንግድ፣ የኢንቨስትመንት ወይም የፍትሐብሔር አለመግባባት ነው፡፡
3. **“የግልግል ዳኝነት ጉባዔ”** ማለት በግልግል ዳኝነት የሚታዩ ጉዳዮችን የሚመራና ውሳኔ የሚሰጥ አካል ነው፡፡
4. **“የግልግል ዳኝነት ውሳኔ”** ማለት በግልግል ዳኝነት የሚሰጥ ውሳኔ ሲሆን እንደሁኔታው ብይኖችንና ትዕዛዛትን ይጨምራል፡፡
5. **“አመልካች”** ማለት ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው አቤቱታ ያቀረበው ወገን ነው፡፡
6. **“ተጠሪ”** ማለት ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው በቀረበው አቤቱታ መሰረት መልስ እንዲሰጥ የተጠራ ሰው ነው፡፡
7. **“ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ”** እና **“ም/ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ”** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ እና ም/ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማለት ነዉ፡፡
8. **“ዳይሬክቶሬት”** እና **“ዳይሬክተር”** ማለት እንደ ቅደም ተከተላቸው የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የፍትሐብሔር ፍትህ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት እና ዳይሬክተር ማለት ነው፡፡
9. **“የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት”** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፌዴራል መንግሥት በጀት የሚተዳደር እና የፌዴራል መንግሥት ሥራዎች የሚከናወኑበት መሥሪያ ቤት ማለት ሲሆን ቅርንጫፎች እና በመስሪያ ቤቱ ስር የተዋቀሩ ተጠሪ መስሪያ ቤቶችንም ያጠቃልላል፡፡

10. **"የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት"** ማለት የፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ድርሻ በሙሉ ወይም በከፊል ያለበት የፌዴራል መንግሥት የልማት ድርጅት ወይም አክሲዮን ማህበር ሲሆን ቅርንጫፎች እና በድርጅቱ ስር የተዋቀሩ ተጠሪ ተቋማትንም ያጠቃልላል፡፡
11. **"የፌዴራል መንግሥት ተቋም"** ማለት የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤት እና የፌዴራል መንግስት የልማት ድርጅትን የሚያጠቃልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡
12. **"ፍርድ ቤት"** ማለት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን በውክልና የተሰጣቸው የክልል ፍርድ ቤቶች ማለት ነዉ፡፡
13. **"አቅም የሌለው ዜጋ"** ማለት ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይለት አቤቱታ የሚያቀርብ የገንዘብ ዓቅም የሌለው የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡
14. በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፀው ሁሉ ለሴትም ተፈፃሚ ይሆናል

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

*ይህ መመሪያ*

1. በግልግል ዳኝነት ሂደት ውስጥ በሚሳተፉ በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች፣ ዓቃብያነ ሕግና ሌሎች ሰራተኞች፣
2. በሁሉም የመንግስት ተቋማት፣
3. የሚካሰሱት ከመንግስት ተቋም ጋር ሆኖ አገልግሎቱን በፍቃደኝነት ለማግኘት ጥያቄ በሚያቀርቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች እና
4. በአቅመ ደካማ ዜጎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 4. <u>የግልግል ዳኝነትን ስለመጀመር</u>

1. ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት እንዲታይለት የሚፈልግ ማንኛውም አመልካች ጥያቄውን በጽሁፍ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ በግልግል ዳኝነት ጉባዔው ለመዳኘት ያለውን ፍቃደኝነት ማመልከት አለበት፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀርበው ማመልከቻ ከክስ ማመልከቻና ከማስረጃ ዝርዝር ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፣
4. በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርበው ጥያቄ ለዳይሬክቶሬቱ በሶስት ቅጂ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ መሰረት አቤቱታ የቀረበበት ቀን የግልግል ዳኝነት ሂደቱ የተጀመረበት የመጀመሪያ ቀን ተደርጎ ይወሰዳል፣

## 5. የግልግል ዳኝነት ጥያቄን ስለመመርመር

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት የቀረበን አቤቱታ ተቀብሎ ለሌላው ወገን መጥሪያ ከመላኩ በፊት ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት መታየት ያለበት ስለመሆን አለመሆኑ ዳይሬክተሩ ውሳኔ ይሰጣል፣
2. ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት መታየት የለበትም የሚል ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ ይህንኑ አቤቱታውን ላቀረበው አካል በጽሁፍ ያሳውቃል፣

## 6. የግልግል ዳኝነት ጥያቄን ለሌላው ወገን ስለመግለጽ

1. ዳይሬክተሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰርት የቀረበውን የክስ አቤቱታ ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት መታየት አለበት የሚል ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ የክስ አቤቱታውን ከነማስረጃዎቹ ለተጠሪ ይልካል፣
2. ተጠሪው የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ በሆነ ጊዜ ዳይሬክተሩ በቅድሚያ የግልግል ዳኝነት ፈቃደኝነት ጥሪ በጽሁፍ ይልካል፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በተላከው ጥሪ መሰረት ድርጅቱ ወይም ግለሰቡ ፈቃደኝነቱን በጽሁፍ የሚገልጽ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር በተመለከተው መሰረት የክስ አቤቱታው ከነማስረጃዎቹ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

## 7. ስለክስ፣ ስለመልስ እና ስለተከሳሽ ከሳሽነት ማመልከቻ አቀራረብ

1. ለግልግል ዳኝነት የሚቀርበው ክስ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ከአንቀጽ 22 እስከ አንቀጽ 33 ድረስ በተደነገጉት ድንጋጌዎች አግባብ ነው፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ለቀረበ ክስ የሚሰጠው መልስ እና የተከሳሽ ከሳሽነት ማመልከች በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ከአንቀጽ 34 እስከ 40 በተደነገገው አግባብ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- ስለግልግል ዳኝነት ጉባዔ

## 8. ስለግልግል ዳኝነት ጉባዔ መቋቋም

1. የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የግልግል ዳኝነት ጉባዔ በዚህ መመሪያ መሰረት ተቋቁሟል፣
2. የጉባዔው ተጠሪነት ለፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የክርክር ጉዳዮች ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ነው፣
3. ዳይሬክቶሬቱ የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ጽ/ቤት በመሆን ይሰራል፡፡

## 9. የግልግል ዳኝነት ጉባዔ አባላት አሰያየም

1. የግልግል ዳኝነት አባላት እንደ አስፈላጊነቱ እና እንደጉዳዩ ውስብስብነት አንድ ወይም ሶስት ሊሆኑ ይችላሉ፣
2. የጉባዔው አባላት በዳይሬክተሩ አቅራቢነት በክርክር ጉዳዮች ምክትል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ይሾማሉ፣
3. የግልግል ዳኝነት ሂደቱ በአንድ ወይም በሶስት የግልግል ዳኛ ይታይ የሚለውን ጉዳዩን በመመርመር ዳይሬክተሩ ይወስናል፡፡
4. የግልግል ዳኝነት ጉባዔውን የስራ ክንውን የሚመዘግብና መዛግብቶችን አደራጅቶ የሚይዝ አንድ ድምጽ የማይሰጥ ባለሞያ በፀሀፊነት በዳይሬክተሩ ይመደባል፡፡

## 10. ነፃነትና ገለልተኝነት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የተሾመ የግልግል ዳኛ ሥራውን በሙሉ ነፃነትና ገለልተኝነት ያከናውናል፣
2. የግልግል ዳኛው በሥራው ሂደት ውስጥ ነፃነቱንና ገለልተኛነቱን የሚፈታተኑ ሁኔታዎች ካጋጠሙት ጉዳዩን ለዳይሬክተሩ በማሳወቅ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አለበት

## 11. የግልግል ዳኝነት አባላት ግዴታዎች

1. የግልግል ዳኝነት ጉባዔ አባላት ለሁለቱም ወገኖች እኩል የመሰማትና ማስረጃ የማቅረብ ዕድል የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡
2. ማናቸውም የግልግል ዳኝነት ጉባዔ አባል በስራው ሂደት ያገኛቸውን መረጃዎች በሚስጢር የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡
3. የግልግል ዳኝነት ጉባዔ ፀሀፊ ሆኖ የሚመደበው ባለሞያ የግልግል ዳኝነት ስራ ሂደቱንና ማስረጃዎችን መዝግቦ የመያዝ፣ መዝገብ የማደራጀትና ሚስጢር የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡

## 12. የግልግል ዳኛን ስለመቃወም

1. በተያዘው ጉዳይ የተመደበው የግልግል ዳኛ ጉዳዩን በነፃነትና በገለልተኛነት ሊያየው የማይችል መሆኑን ተከራካሪዎች በተጨባጭ ማስረጃ አስደግፈው ሊቃወሙ ይችላሉ፣
2. የቀረበው ማስረጃ አሳማኝ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ዳይሬክተሩ ይመረምራል፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ጉዳዩን መርምሮ መቃወሚያው አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ዳይሬክተሩ የተመደበው ዳኛ በሌላ ዳኛ እንዲተካ ሊያደርግ ይችላል፣
4. መቃወሚያ የቀረበበት በመሆኑ ብቻ ጉዳዩን እንዲያይ የተመደበው የግልግል ዳኛ በራሱ ፍቃድ ኃላፊነቱን መተው አይችልም፡፡

## ምዕራፍ ሶስት፡- የግልግል ዳኝነት ስለሚመራበት ሥርዓት

### 13. መሰረቱ

1. የግልግል ዳኝነት ሂደቱ የሚመራው በዚህ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
2. ሂደቱ የሚመራበትን ሂደት ሁለቱ ወገኖች አስቀድመው ተስማምተውበት እንደሆነ ይህን መመሪያ እስካልተቃወመ ድረስ ስምምነታቸው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. በዚህ መመሪያ ወይም በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ያልተሸፈነ ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ከተነሳ አግባብነት ባላቸው ሌሎች የሀገሪቱ ህጎች ይመራል፡፡

### 14. የግልግል ዳኝነቱ የአመራር ሥነ-ሥርዓት

1. በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ተግባራዊ የሚሆነውን ሥነ-ሥርዓት ጉባዔው ይወስናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሰው ቢኖርም ሂደቱ የሚመራበትን ሥነ-ሥርዓት በሚመለከት ጉባዔው ከሁለቱ ወገኖች ጋር ተወያይቶ መወሰን ይችላል፡፡

### 15. የግልግል ዳኝነት ጉባዔ ምልዓተ ጉባዔ

1. የግልግል ዳኝነት ሂደቱ ሁሉም የግልግል ዳኞች ተሟልተው በተገኙበት ይካሄዳል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሰው ቢኖርም በግልግል ዳኝነት ሂደቱ በድምጽ ብልጫ እንዲወሰን የሚያስፈልግ ጉዳይ ካላጋጠመ በተገኙት የግልግል ዳኞች ሂደቱ ሊከናወን ይችላል፡፡
3. ሶስት የግልግል ዳኞች በሚሰየሙበት ጉዳይ አንደኛቸው በተደጋጋሚ ከችሎቱ የሚቀሩ ከሆነ ወይም በሂደቱ ሲሳተፉ ብቁ ሆነው ያልተገኙ እንደሆነ ወይም የስነ ምግባር ችግር ያለባቸው መሆኑን ሰብሳቢው ዳኛ ያወቀ እንደሆነ በጽሁፍ ከኃላፊነታቸው ሊያግዳቸው ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ሲያግድ ጉዳዩን ለዳይሬክተሩ በጽሁፍ አቅርቦ ተተኪ ዳኛ እንዲመደብለት ማድረግ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ስር የተመለከቱት ችግሮች የሚስተዋሉት በሰብሳቢ ዳኛው በሆነ ጊዜ የተቀሩት ዳኞች ጉዳዩን በዝርዝር በመግለጽ ለዳይሬክተሩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 መሰረት ዳይሬክተሩ ማመልከቻውን ከተቀበለ በኋላ ስለነገሩ በማጣራት እውነት ሆኖ ሲያገኘው ምትክ ዳኛ ይመድባል፡፡

### 16. ስለጉባዔው የስራ ቦታ

1. የጉባዔው የስራ ቦታ በዳይሬክቶሬቱ ጽ/ቤት ውስጥ ነው፡፡

2. ዳይሬክተሩ ለጉዳዩ አመራር አግባብ ነው ብሎ ካመነ የጉባዔውን የሥራ ቦታ በጊዜያዊነት ወደሌላ ስፍራ ሊያዛውረው ይችላል፡፡

## 17. የጉባዔው የስራ ቋንቋ

1. የጉባዔው የስራ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡
2. አማርኛ ተናጋሪ ያልሆነ ወገን የራሱን የአማርኛ አስተርጓሚ ይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. ለጉባዔው የሚቀርቡ ማናቸውም የሰነድ ማስረጃዎች የመተርጎም ስልጣን በተሰጠው አካል በአማርኛ ተተርጉመው መቅረብ አለባቸው፡፡

## 18. በግልግል ዳኝነቱ ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ሕጎች

በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ላይ የፍትሐብሔር ሕግ፣ የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ሕግ፣ የንግድ ሕግ እንዲሁም ሌሎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የሀገሪቱ ሕጎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

# ምዕራፍ አራት፡- ስለግልግል ዳኝነት ውሳኔ፣ ስለአፈፃፀሙ እና ስለይግባኝ

## 19. ውሣኔ ስለመስጠትና በድምፅ ስለመለየት

1. በማናቸውም ለግልግል ዳኝነት በቀረበ ጉዳይ ላይ ውሣኔ የሚሰጠው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡
2. ከአብላጫው ድምፅ ውሣኔ የተለየ የጉባዔ አባል ካለ የልዩነት ሀሣቡን በውሣኔው ላይ በግልፅ በጽሑፍ ማስፈር አለበት፡፡

## 20. የግልግል ዳኝነት ውሳኔ ይዘት

1. በግልግል ዳኝነት ጉባዔው የሚሰጠው ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 182 እና 183 ውስጥ የተመለከቱትን ነገሮች እንደ አግባብነቱ የያዘ መሆን አለበት፡፡
2. የጉዳዩ አመጣጥ፣ አስቀድሞ በሌሎች አማራጭ መንገዶች ለመፍታት ተደርጎ የነበረ ጥረት፣ ግራ ቀኙ ይዘውት የነበረውን አቋም እና ልዩነታቸውን እንዴት እንዳጠበቡት እንዲሁም ስምምነት ላይ መድረሳቸው በውሳኔው ላይ መስፈር አለበት፡፡

## 21. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው ውሳኔ አስገዳጅ ስለመሆኑ

በግልግል ዳኝነት ጉባዔው የሚሰጥ ውሳኔ ተፈፃሚና አስገዳጅነት አለው፡፡

## 22. ውሳኔን ስለማብራራትና ስለማረም

1. ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የግልግል ዳኝነት ውሳኔው በደረሰው በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔው እንዲብራራለት ወይም የአፃፃፍም ሆነ የስሌት ስህተት

እንዲታረምለት ወይም ዳኝነት ተጠይቆባቸውና በጭብጥነትም ተይዘው ውሳኔ ሳይሰጥባቸው በተዘለሉ ፍሬ ነገሮች ላይ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለዳይሬክቶሬቱ በጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

2. ዳይሬክተሩ የቀረበው ጥያቄ ለሌላኛው ወገን እንዲደርሰው አድርጎ ሀሳብ ከሰጠበት በኋላ ጉባዔው ተገቢውን እንዲሰራ ያቀርብለታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቀረበውን ጥያቄ ሌላኛው ወገን ከሰጠው ሀሳብ ጋር በማገናዘብ ጉባዔው ተገቢ ነው ብሎ ያመነውን ይወስናል፡፡

## 23. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው በሰጠው ውሣኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

1. በግልግል ዳኝነት ጉባዔ በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተሰጠ በአስር ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻውን ለክርክር ጉዳዮች ም/ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ቅሬታውን አቅርቦ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬት የሚኖረው አካል ውሳኔው በተሰጠው በአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለጠቅላይ ዓቃቤ ህጉ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. በዚህ ዓንቀፅ ንዑስ ዓንቀፅ 1 እና 2 መሰረት በቀረበው ቅሬታ ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነዉ፡፡

## 24. የግልግል ዳኝነት ጉባዔው የሰጠው ውሣኔ ስለሚፈፀምበት ሁኔታ

1. በውሣኔው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን ውሣኔውን ለማስፈፀም የአፈፃፀም አቤቱታ ለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ጉባዔውም በራሱ የተሰጠውን ውሣኔ ያስፈጽማል፡፡
2. በዚህ ዓንቀፅ ንዑስ ዓንቀፅ 1 የተመለከተው ቢኖርም የፍርድ ባለመብት ውሣኔው የሚፈፀምበት የፍርድ ባለዕዳውን የንብረት ዝርዝር አጣርቶ በፅሑፍ ማቅረብ አለበት፡፡
3. ጉባዔው በሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲቀርብ አፈፃፀሙ ለጊዜው ታግዶ ይቆያል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የፍርድ ባለመብት ውሳኔው እንዲፈጸምለት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት፡- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 25. ስለግልግል ዳኝነት ጉባዔው ወጪዎች

1. ጉዳዮችን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ ለተቋሙም ሆነ ለጉባዔው አባላት የሚከፈል ክፍያ አይኖርም፡፡

2. በዚህ ዓንቀፅ ንዑስ ዓንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ጉባዔው ለትክክለኛ ፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያምንባቸውን ወጪዎች ጉዳዩ በልዩ ሁኔታ እንዲመረመርለት በጠየቀው ወገን ይሸፈናል፡፡

3. ጉባዔው በራሱ አነሳሽነት ነገሮች እንዲመረመሩ በሚያዝበት ወቅት የሚወጡ ወጪዎችን ሁለቱ ወገኖች በጋራ ይሸፍናሉ፡፡

4. በግልግል ዳኝነት ሂደቱ ጥቅም ላይ የሚውሉ የፅህፈት መሳሪያዎችና ሌሎች አስፈላጊ ወጪዎችን የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ይሸፈናል፡፡

## 26. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ዳይሬክቶሬቱ የሚመራባቸው የአሰራር ሰነዶች እንደአግባብነታቸው በዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡
2. የግልግል ዳኞችን ምርጫ፣ ሹመትና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱት የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡
3. ይህ መመሪያ ዳይሬክተሩ እንደአስፈላጊነቱ የግልግል ዳኝነት ጉባዔዎችን በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ቅርንጫፍ እና ምድብ ጽ/ቤቶች ከማቋቋም የሚያግደው አይደለም፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ዳይሬክተሩ የሚያቋቁማቸው ጉባዔዎች እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ መሰረት ስራቸውን ይሰራሉ፡፡

## 27. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሥራ አመራር ካውንስል ውሳኔ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል፣ ሊለወጥ ወይም ሊሻር ይችላል፡፡

## 28. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማኑዋል በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሥራ አመራር ካውንስል ተቀባይነት አግኝቶ ከፀደቀበት ከ-----------------ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጌታቸው አምባዬ

ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ